የረቡዕ መስከረም 11 1998 ዓም ( ሴፕቴምበር 21 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## የኢትዮጵያን ሕዝብ ዕድል ማንም የውጭ ኃይል አይወስንም

እንደ ማነኛውም የቀሪው የዓለም ሕዝብ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብም፥ የራሱ ሉዓላዊነት የተከበረ ለመሆኑ የሚያጠያይቅ እንዳልሆነ ብንረዳም፥ በተለያየ ወቅት የባዕዳን ጣልቃ-ገብነት ሀገራችንን ሲያምሳትና ሕዝቡንም ሲያስቸግረው እንደነበር የታወቀ ነው:: ባዕዳን፥ ሀገራችንን ለምን ሁል ጊዜ ትኩር-ጥምድ እንደሚያደርጓት የተለያዩ ምክንያቶች ሊቀርቡ ቢችሉም፥ እነዚህ ምክንያቶች ግን የማነኛውንም ሀገር ሉዓላዊነት ለመድፈር ማጠየቂያ ሊሆኑ የሚችሉ አይደሉም:: ሊሆኑም የሚገባቸውና የሚፈቀድላቸው አይደሉም:: የአንድ ነፃ ሕዝብና ሀገር ሉዓላዊነት በምንም ምክንያት ይሁን በማንም ኃይል ሊደፈር፥ ሊገሰስና ሊዋረድ ከቶ አይገባውም:: ቀደም ባለው ጊዜ የአውሮጳ ቅኝ ገዢዎች ሀገራችንን ለመውረርና ለማንበርከክ ሞክረው ሀፍረትን ተከናንበው ተመልሰዋል:: ቀደም ሲል በዘመናት የተሞከረውን የባዕዳን በሀገራችን የጣልቃ ገብነት ሙከራ ሁሉ ሊከሽፍ የበቃው፥ በአንድ መሠረታዊ ምክንያት እንደሆነ ታሪክ ምስክር ነው:: ይህም ምክንያት የሕዝቧ በመተባበር መቆምና አልገዛም ባይነት ባኅርይ ነበር:: በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ የጦርነቱ ሰለባ የነበረችው ሀገራችን ፥እንደ ሌሎቹ የቅኝ ግዛት ሀገሮች ሁሉ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት እንደትሆን ተፈርዶባት ነበር:: ያንን ፍርድ ገልብጠው ወራሪውን ኃይል በማባረር ነፃነቷን ያስመለሱላት ግን አርበኞቿ ነበሩ:: ይህን ለማድረግ ደግሞ ወደ ዓለም ፍርድ ቤት በመሄድ የክስ ማመልከቻ አላቀረቡም:: የኢትዮጵያን ዕድል መወሰን የሚገባው እራሱ ሕዝቧ ለመሆኑ በተግባር አስመስክረው፥ በታሪክ አስመዝግበው ለተተኪው ትውልድ አስረክበው አልፈዋል:: ይህንን አኩሪ ታሪክ የዛሬው ትውልድ እንደ መመሪያ ሊጠቀምበት ይገባል::

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜም በኋላ፣ እንግሊዞች፥ ዐረቦችና አሜሪካኖች በመፈራረቅ የኢትዮጵያን ዕድል ለመወስን የተለያዩ ሙከራዎች እንዳደረጉባት የሚካድ አልነበረም:: ለሀገሩና ሉዓላዊነቱ ቀናዔ የነበረው ትውልድ ሳይበገር በመቅረቱ ሳይሳካላቸው ቀይቷል:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሰቆቃ ማኅፀን የተወለደው የየካቲቱ 66 ዐብዮት የኢትዮጵያ አንጡራ ዐቢዮት እንደነበረ ብናምንም፥ ጥቂት አምባገነኖች ለቀድሞዋ ሶቬየት ኅብረት መሪዎች አሳልፈው በመስጠት የብሔራዊ ክኅደት ወንጀል ፈፅመዋል:: የሶቬየት ሩሲያ መሪዎችም ለአስራ ሰባት ዓመታት ሀገራችንንና ሕዝባችንን እንዳሻቸው ሲያደርጉ ቆይተው፥ እንድትፈረካከስም ምክንያት ሆነው በመጨረሻ ጓዛቸውን ጠቅለለው ሄደዋል::

የሶቬየትን በሀገራችን ጣልቃገብነት ለመዋጋት ከፍተኛ መስዋዕትን የጠየቀ ትግል ተደርጎ ከኢትዮጵያ ሊወጡ ቢችሉም፥ እናም ደግሞ፥

አገልጋያቸው የነበረው መንግሥቱ ኃይለማርያም ዱካቸውን ተከትሎ ቢፈረጥጥም፥የሀገራችን መከራ በዚህ ሊያከትም አልቻለም። ከሶቬየት ኅብረት መፈረካከስ በኋላ፥ የዓለም የፖለቲካ መልከአምድር በመሠረታዊ መልኩ ቢለወጥም፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን አሁንም ከውጭ ጣልቃ ገብነት ነፃ ልትወጣ አልሆነላትም። በተለይም በምዕራብያውያን ምርቃትና ድጋፍ በሥልጣን ላይ የወጣው ጠባብ ብሄርተኛ ቡድን፥ በግንቦት 1983 ዓም ሎንዶን ላይ በተደረገው የምዕራባውያን ሽረባና ጣልቃ ገብነት የሀገራችን ኅልውና ከመኖር ወደ አለመኖር ከመቅፅበት ሊለወጥ ቻለ። ይህ ሊሆን የበቃው፥ ለሀገር፥ ለሕዝብ፥ ለታሪክ፥ ለባህል፥ ለነፃነትና ለሉዓላዊነት ግድ የሌለው ጎጠኛ ብድን ሥልጣን ላይ በመምጣቱ ብቻ ነው። ይህ ክስተት ደግሞ በበኩሉ፥ ምዕራባውያን በሀገራችን ውስጥ ጣልቃ በመግባት እንዳሻቸው እንዲፈነጩ መልካም አጋጣሚ ሰጥቷቸዋል።

ከዚህም አልፈው ተርፈው፥ ሀገሪቱ ማንም ተቆርቋሪና ቀናዔ የሌላት መሆኗን በመረዳታቸው እነሆ ይኸው ዛሬ፥ ሕዝብ በምርጫው አንቅሮ የተፋውን ቡድን፥ የሕዝቡን ድምፅ ሰርቆ አቸንፌያለው ብሎ ከሥልጣን ላለመውረድ መወሰኑን በመደገፍ፥ ተቃዋሚ ድርጅቶች ተንበርክከው እንዲገዙለት ተፅዕኖ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ይህ ድርጊት በታሪኩ ኩሩና ጀግና የነበረውን ሕዝብ ሉዓላዊነት ከመግፈፉ በላይ፥ ተቀባይነትም ሆነ ሕጋዊነት የሌለው ነው። የምዕራብያውያኑን ተፅዕኖ በመቀበል ለወያኔ መሪዎች ተንበርክኮ መገዛት የሚቻለው፥ ኢትዮጵያውያን እናቶች፥ ጀግና ጀግና ልጆች መውለድ ሲያቆሙ ብቻ ይሆናል። ኢትዮጵያ ሀገራችን፥በባዕዳን ጣልቃ ገብነትና ውሳኔ ልትተዳደር የምትበቃው፥የኢትዮጵያ ጀግኖች አልቀው-ተመትረው፥ የኢትዮጵያ እናቶች፥ ከል ሲለብሱ፥ ገመድ ሲታጠቁ፥ ማህፀናቸው ሲደርቅና፥ የወላድ መካን ሆነው ሲቀሩ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ህግ ስለማይፈቅድ፥ የሚሆን አይደለም። ጀግኖች መፈጠራቸው አይቀሬ ነው። ለሀገሩ፥ ለታሪኩ፥ ለሰብዕናው፥ ለማንነቱ፥ ለነፃነቱና ለሉዓላዊነቱ ተቆርቁሮ የሚነሳ ትውልድ ይነሳል፥ ተነስቷልም። ያ ክስተት ሲመጣ ደግሞ፥ እንደ ቀድሞ ጀግኖች አባቶቹ/ እናቶቹ የሀገሩን ክብር፥ ኩራትና የነፃነት ልዕልና አክብሮ የሚያስከብር ትውልድ፥ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን የሚያረጋግጥበት ወቅት ሩቅ አይሆንም። ዛሬ፥ የትላንትናው ጀግና ትውልድ ባኅርይና ሀሞት አገርሽቶበታል።

" ዳመናው ሲደምን ይወረዛል ገደል፥
ይዘገያል እንጅ መች ይረሳል በድል፥
ወተት ይሸፍታል እንኳን ሕዝብ ሲበደል" የሚባለውም ለዚህ ነው።

ዛሬም እንደ ትላንቱ፥ ምዕራባውያኑ እንዲሁም ሌሎች ባዕዳን ጭምር፥ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነቱና ለዴሞክራሲ መብቱ የሚያደርገውን ትግል ለማኮላሸት ተባብረዋል። መለስ ዜናዊንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣና ፍርድ ሊከላከሉለት ወስነዋል። ይህ የያዙት ርምጃ ግን የሚያዋጣ አይደለም። ምዕራባውያኑ ይህን አደገኛ ውሳኔ

የወሰዱበትን ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል:: የዓለም አቀፍን ህግጋት ሁሉ በመጣስና ራሳቸውንም በታሪክ የሚያስተዛዝባቸውን ስህተት በመፈፀም፥ መለስ ዜናዊን ለማዳን የሚያደርጉትን መፍጨርጨር፥ ምክንያት እኛ ኢትዮጵያውያን እንገነዘበዋለን:: ይኸውም፥ ምን ጊዜም ቢሆን፥ ወደፊት፥ እንደ መለስ ዘናዊ ዓይነት ታማኝ አገልጋይ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ የማያገኙ መሆናቸው ነው:: ምንም ቢሆን ምን፥ ወደፊት በሀገራችን፥ ለምዕራባውያን ጣልቃ ገብነት ሀገሪቱን አመቻችቶ በማቅረብ፥ እንደ መለስ ዓይነት ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሚል መሪ ነኝ ባይ ሎሌ ይመጣል ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማመን ይቸገራል::

በዚህም ተባለ በዚያ፥ ሀገራችን ከዘረኛው የወያኔ አገዛዝም ሆነ፥ ከበላይ ጠባቂዎቹ የውስጥ ጣልቃ ገብነት ነፃ መውጣት አለባት ከተባለ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብና ተቃዋሚው ኃይል የሚከተሉትን የነፃነትና የማንነት ማረጋገጫ ርምጃዎች ሊወስዱ ይገባል::---

1) ከዚህ ከያዝነው መስከረም ወር በኋላ ጎራው የሚለይለት የተቃዋሚው ኃይል፥ ለምዕራቡ ተፅዕኖ በመንበርከክ ወደ ወያኔ ፓርላማ የሚገባው ገብቶ፥ ለመግባት ያልወሰነው ደግሞ፥ ነጥሮ በመውጣት ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይል ፈጥሮ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጋር አብሮ እንዲቆም ይጠበቅበታል:: ታሪካዊ ተልዕኮውም ይኸው ነው::

2) በኢትዮጵያ የፖሊቲካ ኃይላት አሰላለፍ፥ የሚከተለውን ቅርፅ ይይዛል:: በአንድ በኩል፥ ወያኔና የሕዝባቸውን ዕምነት በመካድ አብረውት የቆሙት ክፍሎች ሲሆኑ፥ በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝባቸውንና የሀገራቸውን ዕምነት ሳይክዱ፥ በዓላማቸው የፀኑ፥ ለውጭ ተፅዕኖ ያልተንበረከኩ፥ የሃገራችውን ዘላቂ ጥቅምና ጎልውና ያስቀደሞ ድርጅቶች ይሆናሉ:: በያዙት ዓላማ በመፅናት ለዴሞክራሲና ለሕዝብ ሉዓላዊነት የሚያደርጉትን ትግል መቀጠል ይጠበቅባቸዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎናቸው እንደተሰለፈም ማወቅ አለባቸው::

3) የኢትዮጵያ ሕዝብም በበኩሉ፥ ዛሬም እንደጥንቱ – እንደጧቱ – በብሄረሰብና በሃይማኖት፥ በመደብም ይሁን በሌሎች ሰው ሰራሽ ልዩነቶች ሳይከፋፈል፥ ብሎም ለወያኔ ዕኩይ ተግባር ሳይበገር፥ አንድነቱን አጥንክሮ በመታገል የተቃጣበትን የውጭ ጣልቃ-ገብነትና ተፅዕኖ ማክሸፍ አለበት:: አሁን በያዘው መልኩ አልገዛም ባይነቱን በተግባር ማሳየት ይኖርበታል:: እራሱ ታግሎ ራሱን ነፃ ካላወጣ ማንም ነፃ እንደማያደርገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለፈው ታሪኩ በሚገባ ስለሚያወቅው፥ በዚህ ረገድ የማንንም ቅስቀሳና አስተዋሽነት የሚያስፈልገው መሆኑን በሚገባ እናውቃለን::

4) ምዕራባውያኑ፥ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መጣላት፥ በመጨረሻ የራሳቸውን ስትራተጂያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን አውቀው-ተረድተው በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን የተሳሳተ ፖሊሲ

እንደገና እንዲመረምሩ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በህጋዊ መልክና ትግል በማካሄድም ሊጠይቃቸው፣ ሊነግራቸው ይገባል። አሁን የወሰዱት አቋም ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚጎዳ መሆኑን ሊያውቁት ሊነገራቸውም ይገባል። በጠመንጃ ኃይል የመጣ ከፋፋይ ቡድን በኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ የተሻረ በመሆኑ ህገ-ወጥ መሆኑን በአፅንኦት ሊነገራቸው ያስፈልጋል። የአምባገነኖች ጥርቃሞ የሆነውም የአፍሪካ ኅብረት በማያገባው ገብቶ ከመለስ ዜናዊ ጎን መቆሙ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የሚያስጠይቀው መሆኑን ሊያወቅው ይገባል።

5) በአራተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰውን አደገኛ የባዕዳን ጣልቃ ገብነትና ተፅዕኖ ለመቋቋም፥ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን/ያት ምሁራን የተለየ ኃላፊነትና ተልዕኮ እንዳለባቸው ልናስታውስ እንፈልጋለን። በዓለም የተሰራጩት ምሁራን በሀገራቸው ላይ የተጫነውን ከባድ የምዕራባውያኑን ጣልቃ ገብነት አደገኛነትና ጎጅነት በመዘርዘር ባልተቋረጠ የማጋለጥ የማስረዳት ዘመቻ ላይ መሰማራት አለባቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ በሚያደርገው የዴሞክራሲና የሉዓላዊነት ማስከበሪያ ትግል ከጎኑ እንዲቆሙ ይጠብቃቸዋል። ጥሪም ያስተላልፍላቸዋል። ይህንን ብሔራዊ ጥሪ በአስቸኳይ መመለስ ይዋል ይደር ሊባል የሚችል አይደለም።

በበኩላችን የሀገራችንን ዕድል የሚወስነውያው ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ እንጅ ማንም ባዕዳን የሚመለከተው እንዳልሆነ ስለምናምን፥ ትግላችንን ከሕዝቡ ትግል ጋር አስተባበረን እንቀጠላለን።